የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፴
አዲስ አበባ መጋቢት ፲፱ ቀን ፲፱፻፺፪

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

6[th] Year No. 30
ADDIS ABABA - 28[th] March, 2000

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፷፮ /፲፱፻፺፪ ዓ·ም·
የውጭ ሀገር ዜጎች በኢትዮጵያ ፊልም ስለሚያነሱበት ሁኔታ የወጣ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........................ ገጽ ፩ሺ፪፻፹፬

## CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 66/2000
Film Shooting Permit Council of Ministers Regulations ............................................ Page 1284

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፷፮/፲፱፻፺፪
### የውጭ ሀገር ዜጎች ኢትዮጵያ ውስጥ ፊልም ስለሚያነሱበት ሁኔታ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ መሠረት የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የውጭ ሀገር ዜጎች በኢትዮጵያ ፊልም ስለሚያነሱበት ሁኔታ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፷፮/፲፱፻፺፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ ደንብ ውስጥ፡

፩· "ሚኒስቴር" ማለት የማስታወቂያና ባሕል ሚኒስቴር ነው፡

፪· "ፊልም " ማለት በሴሉሎስ ወይም በማግኔቲክ ቴፕ የሚቀረጽ ተንቀሳቃሽ ሥዕል ነው፡

፫· "ተራኪ ፊልም" ማለት በልቦለድ ድርሰት ላይ ተመስርቶ ተዋንያንን በማሳተፍ የሚቀረጽ ፊልም ነው፡

፬· "ዘጋቢ ፊልም" ማለት ተፈጥሮን፡ ባህልን፡ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን እና የመሳሰሉትን ነገሮች በቴሌቪዥን፡ በሲኒማ፡ ወይም በሌሎች የኤሌክትሮኒክስ ስክሪን ማስተላለፊያዎች ለማሰራጨት ዓላማ የሚቀረጽ ፊልም ነው፡

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS NO. 66/2000
### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE ISSUANCE OF PERMIT TO FOREIGNERS FOR SHOOTING FILMS IN ETHIOPIA

These Regulations are issued by the Council of Ministers Pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995.

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as "Film shooting permit Council of Ministers Regulations. No. 66/2000."

2. *Definitions*

In these Regulations:

1) "Ministry" means the Ministry of Information and Culture;
2) "Film" means a mobile picture recorded by cellulose or magnetic tape;
3) "Feature Film" means a fictional film in which film actors participate;
4) "Documentary Film" means a film recorded with the objective of broadcasting or disseminating natural, historical, cultural, political, economical, social conditions and other factual materials through television, cinema or other electronic screen transmissions;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2·30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፭· "የፊልም ማንሳት ፈቃድ" ማለት በዚህ ደንብ መሠረት በተወሰነ ጊዜና ቦታ ተራኪ ወይም ዘጋቢ ፊልም ለማንሳት ብቻ ለሚመጡ የውጭ ዜጎች በሚኒስቴሩ የሚሰጥ ፈቃድ ነው።

፫· የተፈጻሚነት ወሰን

የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች፡

፩· ኢትዮጵያ ውስጥ የፊልም ተቋም እንዲያቋቁሙ ቋሚ ፈቃድ ከተሰጣቸው ሰዎች በስተቀር ዓላማቸው ትርፍ የሆነ ወይም ያልሆነ ተራኪ ወይም ዘጋቢ ፊልም ለማንሳት በሚመጡ የውጭ ዜጎች ላይ፡

፪· በሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች፡

ተፈጻሚ ይሆናሉ።

፬· ዓላማ

የደንቡ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡

፩· በውጭ ዜጎች የሚካሔደው የፊልም ማንሳት ሥራ የሀገሪቱን ታሪክ፡ ባህል፡ የተፈጥሮ ውበት፡ ሀብት፡ ፖለቲካዊ ፡ ኢኮኖሚያዊ፡ ማህበራዊ ሁኔታ እና የመሳሰሉትን ለውጭው ዓለም በማስተዋወቅ ጉልህ ሚና የሚጫወት ስለሆነ ሥራው የሚመራበትን ሥርዓት ግልጽና ቀልጣፋ በማድረግ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፡

፪· የሀገሪቱ ዜጎችና ድርጅቶች ከሚነሳው ፊልም ማግኘት የሚገባቸውን መብትና ጥቅም ማስከበር፡

፫· የፊልም ማንሳቱ ሥራ የሀገሪቱን ሕጎች እና የሕዝቦቿን ባህል በማክበር እንዲካሔድ ማድረግ።

፭· ፈቃድ ስለማስፈለጉ

ኢትዮጵያ ውስጥ ተራኪ ወይም ዘጋቢ ፊልም ለማንሳት የሚፈልግ ማንኛውም የውጭ ዜጋ ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል።

፮· ፊልም ለማንሳት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

፩· ኢትዮጵያ ውስጥ ፊልም ለማንሳት የሚፈልግ የውጭ ዜጋ ሥራው ከሚጀምርበት ከ፲ ቀን በፊት ማመልከቻውን ለሚኒስቴሩ በጽሑፍ ማቅረብ ይኖርበታል።

፪· ማመልከቻው በተለይም የፊልሙን ዓላማና ርዕስ፡ ፊልም ማንሳቱ የሚቆይበትን ጊዜ፡ ፊልም ማንሳቱ የሚካሔድበትን ትክክለኛ ሥፍራ እና ለፊልሙ ሥራ የሚውለውን ጠቅላላ ወጪ እንዲሁም ከጠቅላላው ወጪ ውስጥ ኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ ላይ የሚውለውን ገንዘብ መግለጽ ይኖርበታል።

፫· አመልካቹ ከማመልከቻው ጋር፡ .

ሀ) ተራኪ ፊልም ከሆነ የፊልሙን ስክሪፕት አንድ ቅጂ ከነአጭር መግለጫው ወይም ዘጋቢ ፊልም ከሆነ አጭር መግለጫውን፡

ለ) በፊልሙ ውስጥ ኢትዮጵያዊ ገጸ ባህርይ የሚካተት ከሆነ ግለሰቡ ወይም ሕጋዊ ወራሾቹ የማይቃወሙ መሆኑን የሚያመለክት ውሎችንና ሰነዶችን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ሰነድ፡

ሐ) በኢትዮጵያዊና በውጭ ዜጋ በጋራ የሚሰራ ፊልም ሲሆን የእያንዳንዱን ወገን ግዴታና ኃላፊነት የሚያመለክት በሁለቱ መካከል የተደረገ ስምምነት ፡ እና

መ) በፊልም ሥራው ላይ የሚሰማሩትን ሰዎች ዜግነት ፡ የፓስፖርቱን ቁጥር ፡ ፓስፖርቱን የሰጠው አገር ፡ ቋሚና ጊዜያዊ አድራሻ ፡ እንዲሁም ሌሎች በሚኒስቴሩ የሚጠየቁ መረጃዎችን፡

አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል ።

፯· ፈቃድ ስለመስጠት

፩· ሚኒስቴሩ በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፮ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው መቅረባቸውንና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፪ ውስጥ የተወሰነው የፈቃድ ክፍያ መፈጸሙን በማረጋገጥ ማመልከቻው በቀረበለት በ፫ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ ፈቃድ ይሰጣል ።

5) "Film Shooting Permit" means a permit issued under these Regulations by the Ministry to foreigners who come only to shoot a particular feature or documentary film within specific period of time and place.

3. *Scope of Application*

The provisions of these Regulations shall apply:

1) on foreigners who come to shoot films either for profit or non profit purpose, with the exception of film establsihments which are permanently established and licenced in Ethiopia;
2) in all Regions of Ethiopia.

4. *Purpose*

The purposes of these Regulations are:

1) To create conducive environment for the film shooting, with the understanding of its preminent role in publicizing the history, culture, natural beauty, resources, political, economic, social and other activities of the country to the world;
2) To ensure that the rights and benefits of the country's nationals and organizations are protected during the film shooting;
3) To ensure that the culture and laws of the country are respected.

5. *Requirement of permit*

A foreigner wishing to shoot a feature or documentary film in Ethiopia shall obtain a permit from the Ministry.

6. *Application for shooting films*

1) A foreigner wishing to shoot films in Ethiopia shall submit his application to the Ministry not later than ten (10) days prior to the day on which he is due to commence filming.
2) The application shall contain, among other things, the purpose and title of the film, duration of the shooting and the exact location where it takes place and the total production cost of the film as well as the portion that will be used within Ethiopia.
3) The applicant shall submit together with his application the following:
   (a) A copy of the film script along with its synopsis for feature films or synopsis for documentary films;
   (b) In case an Ethiopian personality is portrayed in the film as a character, a copy of a document of no objection from such person or his heirs, certified by an organ legally empowered to approve contrats and documents;
   (c) In case of a co-production by an Ethiopian and a foreigner, an agreement indicating the responsibilities and liabilities of each party;
   (d) The nationality of the filming crew, the passport number, the country issuing the passport, their permanent and temporary addresses as well as other information as may be required by the Ministry.

7. *Issuance of permit*

1) The Ministry shall, upon ascertaining the fulfilment of the requirement laid down under Article 6 of these Regulations and payment of the permit fees determined under Article 12 of these Regulations, issue a permit to the applicant within 3 days.

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት በተሰጠ ፈቃድ ላይ ከተገለጹ ቦታዎች መካከል ፊልም ለማንሳት የተከለከሉ ቦታዎች ካሉ ለመከልከል ሥልጣን ያለው አካል መብት የተጠበቀ ነው ።

፰· ስለ በረራ ፈቃድ

፩· አመልካቹ ለፊልም ማንሳቱ ሥራ አይሮፕላን መጠቀም ከፈለገ ከኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን የበረራ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል ።

፪· አመልካቹ ከፈለገ የበረራ ፈቃድ ማመልከቻውን በሚኒስቴሩ አማካኝነት ሊያቀርብ ይችላል ፤

፫· ለፊልሙ ሥራ አይሮፕላን ለመጠቀም የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ከተገኘ የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን ማመልከቻ በቀረበለት በ፲ ቀናት ውስጥ የበረራ ፈቃድ መስጠት አለበት ፤ ጥያቄው ተቀባይነት የሌለው ከሆነም ባለሥልጣኑ ውሳኔውን ለአመልካቹ ወይም ለሚኒስቴሩ በጽሑፍ ያስታውቃል።

፱· የአመልካቹ ግዴታ

አመልካቹ ከዚህ በታች የተመለከቱት ግዴታዎች ይኖሩታል፣

፩· የተሰራውን ፊልም ሁለት የቪ·ኤች·ኤስ· ቪዲዮ ካሴት የእንግሊዝኛ ቅጂ ለሚኒስቴሩ የማስረከብ ፤

፪· በግንባር በመቅረብ በፈቃድ ግዴታው መሠረት ለመሥራትና የአገሪቱን ሕግ ለማክበር ግዴታ የመግባት ።

፲· ፈቃድን ስለመሰረዝ

በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፱/፪/ በተመለከተው መሠረት ባለፈቃዱ የገባውን ግዴታ ያላከበረ እንደሆነ ሚኒስቴሩ ፈቃዱን ሊሰርዝበት ይችላል ።

፲፩· የቀረጥ ነፃ መብት

፩· አመልካቹ ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣቱ በፊት ይዟቸው የሚመጣውን ለፊልሙ ሥራ አገልግሎት የሚውሉ መሣሪያዎችን ዝርዝር ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለበት ።

፪· አመልካቹ በዝርዝሩ የተመለከቱትን እቃዎች ከአገር እንደሚያስወጣ ግዴታ ሲገባም እነዚህ መሣሪያዎች የጉምሩክ ቀረጥ ሳይከፈልባቸው እንዲገቡ ይደረጋል ።

፲፪· ስለ ፈቃድ ክፍያ

፩· ኢትዮጵያ ውስጥ ፊልም ለማንሳት የሚፈልግ የውጭ ዜጋ ከዚህ የተመለከተውን የፈቃድ ክፍያ ለሚኒስቴሩ ይከፍላል ፡

ሀ) ለፊልሙ ሥራ ከሚወጣው ወጪ ለመጀመሪያ ብር ፩፻ሺ /አንድ መቶ ሺህ ብር/ ፡ ብር ፩ሺ /አንድ ሺህ ብር/፡ እና

ለ) ከብር ፩፻ሺ /አንድ መቶ ሺህ ብር/ በላይ ለሆነው ለተጨማሪው የፊልም ሥራ ወጪ ደግሞ ተጨማሪ ዐ·፪ በመቶ (ዜሮ ነጥብ ሁለት ፐርሰንት) ።

፪· የፊልም ማንሳቱ ሥራ የሚካሄደው ፊልም ለማንሳት ክፍያ በሚያስከፍል ቦታ የሆነ እንደሆነ በሚመለከተው አካል የሚጠየቀውን ክፍያ መክፈል ይኖርበታል ።

፲፫· መመሪያ ስለማውጣት

ሚኒስቴሩ ፡ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች በሚገባ ተግባራዊ ለማድረግ መመሪያዎችን ለማውጣት ይችላል ።

፲፬· ውክልና ስለመስጠት

ሚኒስቴሩ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ማናቸውም የፊልም ማንሳት ፈቃድ የተሰጠባቸው ግዴታዎች መጠበቃቸውን ለማረጋገጥ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዲችሉ ውክልና ሊሰጥ ይችላል ።

2) Where there are locations prohibited for filming among areas which are indicated in the permit issued in accordance with Sub Article (1) of this Article, the power of the concerned institution to prohibit filming is reserved.

8. *Flight Permit*
   1) Where an applicant wishes to use an aircraft for shooting a film, he shall obtain a flight permit from the Ethiopian Civil Aviation Authority.
   2) An application for a flight permit may be made through the Ministry upon the request of the applicant.
   3) Where the application to use an aircraft for the film shooting is found acceptable, the Ethiopian Civil Aviation Authority shall issue the flight permit within 10 days from the date of submission of application. Where the Authority rejects the application, it shall notify the applicant or the Ministry, in writing, its decision thereof.

9. *Obligations of the applicant*
   The Applicant shall have the following obligations:
   1) To submit to the Ministry two English VHS Video cassette copies of the film produced;
   2) To appear in person and sign an undertaking to adhere to the conditions of permit and respect the laws of the country.

10. *Revocation of permit*
    A permit may be revoked by the Ministry if the undertaking signed by the permit holder in accordance with Article 9 (2) of these Regulations has not been observed.

11. *Exemptions*
    1) The applicant shall submit to the Ministry a list of equipment necessary for shooting film before his arrival.
    2) Such equipment shall then be imported duty-free on the undertaking that same will be re-exported on departure.

12. *Permit Fee*
    1) A foreigner applying for shooting film in Ethiopia shall pay to the Ministry a permit fee as follows:
       (a) Birr, 1,000.00 (one thousand birr) for the first Birr, 100,000.00(one hundred thousand birr) of the production cost; and
       (b) 0.2% on the additional cost of production over and above Birr, 100,000.00.
    2) Where Filming takes place in location where filming fees are charged, the applicant shall pay the rquired fee to the relevant body.

13. *Issuance of Directives*
    The Ministry may issue directives necessary for the proper implementation of these Regulations.

14. *Delegation*
    The Ministry may delegate the concerned Federal and Regional Government institutions to conduct follow-up and inspection work in order to ensure the observance of the conditions to which the film shooting permit is given.

፲፭· ቅጣት

የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ተላልፎ የተገኘ ሰው አግባብ ባለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ድንጋጌ መሠረት ይቀጣል ።

፲፮· ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ መጋቢት ፲፱ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

15. *Penality*

Whosoever violates the provisions of these Regulations shall be punishable in accordance with the relevant provisions of the penal code.

16. *Effective date*

These Regulations shall enter into force as of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 28th day of March, 2000.

MELES ZENAWI
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATI
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE